# የተላላኪው ጋዜጠኛ ምስጢሮች

ታሪኩ አባዳማ ሐምሌ 2001

ወያኔ እና ሻአቢያ በደርግ ዘመን የተዋጣለት የሰርጎ ገብ ሥራ ማከናወናቸውን ብዙዎች ገልፀውታል። በወታደራዊ ተቋማት፣ በደህንነት እና በሁሉም መንግስታዊ እና ማህበራዊ መዋቅሮች ውስጥ የተሰገሰጉት የወያኔ አባላት ተጨባጭ ውጤት ላይ ያነጣጠረ የግዝገዛ ተግባር አከናውነዋል። የርስ በርስ ጦርነቶች ብዙውን ግዜ እንደዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ድርጊቱ አንዱን ደካማ ሌላውን ጠንካራ አድርጎ የሚያሳይ መመዘኛ አይደለም። ይሁንና ጥቂት የማይባሉ ሰርጎ ገቦች በደረግ ተደርሶባቸው በፍየል ወጠጤ መሰናበታቸው የሚታወቅ ቢሆንም ብዙዎቹ ግን እንኳን ሊደርስባቸው ቀርቶ በሹመት ላይ ሹመት ደርበው እነሱ ራሳቸው ሰርጎ ገብ መንጣሪ የሆኑበት ድራማ ነበር። በተለይ ኢሠፓ በተሰኘው የደርግ ፓርቲ ውስጥ የወሳኝነት ወንበር የተሰጣቸው ሰርጎ ገቦች አፍራሽ ተልዕኳቸውን በብቃት ለመወጣት እንደበቁ አያጠራጥርም። ኩሩ ኢትዮጵያዊ የነበሩ የትግራይ እና ኤርትራ ተወላጆችን በከሀዲነት ወይም የወንበዴ ተባባሪነት እያስመሰከሩ እና እየመሰከሩ እንዲወገዱ ያስደርጉ እንደነበር ሰምቻለሁ። እንደኔ ላለው ጥሮ ግሮ አዳሪ የቱ የቱ እንደሆነ በቅጡ ለመመስከር የማይመችበት ዘመን።

ወያኔ ኤርትራውያንን እንደ ድንች እየጫነ መረብ ላይ መዘርገፍ በተያያዘበት የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ኤርትራውያንን ሰብስባችሁ ወደ አዲስ አበባ ላኩ የሚል መልእክት የደረሰው አንድ ክልል ትግሪኛ ተናጋሪውን ሁሉ በሌሊት ከየቤቱ ሰብስቦ በጭነት መኪና ላይ ማጨቅ ይጀምራል። ታዲያ የትግራይ ተወላጅ ነን የሚሉት በደምፍላት 'ጉዳዩ እኛን አይመለከትም … ' እያሉ አፈሳ ለሚያደርጉት ተቃውሞ ያሰማሉ። የአፈሳው መሪዎች በበኩላቸው 'እኛ ማን ምን እንደሆነ የምናጣራበት መንገድ የለንም … እዚያው አዲስ አበባ ስትደርሱ አጣርተው ይለዩዋችሁ' የሚል መልስ ይሰጧቸው እነደነበር ይነገራል።

ዛሬ የምታነቡት እውነተኛ ታሪክ ነው። በዚህ ታሪክ ሂደት ውስጥ የተሳተፉ ግለሰቦች ብዙዎቹ ዛሬም በህይወት ያሉ ይመስለኛል። በተለይ የሞት ፍርዱን ቃሊቲ ሆኖ እየተጠባበቀ ያለው የቀድሞው የደህንነት ሚኒስትር ተስፋዬ ወልደሥላሴ በስቅላት ይሁን በተቅማጥ ከመሞቱ በፊት ለጥቆ በሚቀርበው ታሪክ ዙሪያ የበለጠ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችላል የሚል እምነት አለኝ።

ዛሬ ይህን የምፅፈው የታሪኩ ዋንኛ ተዋናይ የነበረውን ወታደራዊ መኮንን ባንድ አጋጣሚ በባዕድ አገር አግኝቼው ማስታወሻ እንድይዝ በጠየቀኝ መሠረት ያቆየሁትን ሲሆን በራሴ የሥራ መስክ ያገኘሁት እና ከዚህ ታሪክ ጋር ዝምድና አላቸው ብዬ የገመትኩትን እዚህ እና እዚአ አክዬበታለሁ።

ይህን ታሪክ ዛሬ ለምን መፃፍ አስፈለገ ለሚለው በቂ መልስ የለኝም - ይሁንና በዚህ ትረካ ውስጥ ስማቸው ከሚነሱት ግለሰቦች አንዱ ሰለሞን አስመላሽ በቅርቡ 'አጋዚ' በሚል ርዕስ የወጣ ቪዲዮ ማዘጋጀቱን ሳይ ይህ ሰው እስከመቼ እንዳቆሰለን ይኖራል የሚል ብርቱ ስሜት ውስጤን ወረረው። ግለሰቡ የሚጠላም የሚወደድም አይደለም - ዝርክርክ ቦዘኔ ነው። ይሁንና አድራጎቱ እንዲህ እንደ ዋዛ ተገፍቶ የሚታለፍ ሆኖ አላገኘሁትም። ለወያኔ እና ሻአቢያ ከዋለው ውለታ አኳያ ብዙ ሹመት በሰጡት ነበር። ለዚያ የሚያደርስ ብቃትም ተክለ ሰውነትም እንደሌለው ስለሚያውቁ ይመስለኛል እንዲሁ እንደ እቃ እየተጠቀሙበት የአረቂ እና ሲጋራ ሀራራውን አሸንፎ እንዲያድር የፈቀዱለት።

በመሠረቱ 'አጋዚ' በትግራይ ተወላጆች ብቻ የተገነባ የወያኔ ፈጥኖ ደም አፍሳሽ ጦር እነደሆነ የማያውቅ ያለ አይመስለኝም። 'አጋዚ ናዚ' በሚል ርዕስ ስንኝ ተቋጥሮ ማንበቤ ትዝ ይለኛል። አጋዚ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ከባድ መሣሪያ ሳይቀር ተኩሶ ለመግደል ቅንጣት የማያመነታ ፣ የራሱን ሰላማዊ ዜጎች እንደ ባዕድ ጠላት የሚቆጥር 'ሰው በላ' የጠረባ ጦር መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያውቃል። የወያኔ እኩይ ተፈጥሮ በሚገባ የሚገለፅበት ሕያው አካል ቢኖር 'አጋዚ' ዋንኛው ነው። ለብዙሀን ዜጎች አጋዚ ማለት ጭካኔ ፣ ኢሰብአዊነት ፣ አውሬነት ማለት ነው።

## 1981 (እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር)

አገሪቱ በጦርነት ደመና ውስጥ ከተጋረደች አመታት ያለፉ ቢሆንም ይህ ወቅት የወያኔ እና የሻቢያ ሠራዊት እጅግ አስጨናቂ በሆነ ፍጥነት ወደ መሀል እየገሰገሱ የነበረበት ነው። በ1981 ደርግ የተገንጣይ አስገንጣዮችን ወታደራዊ ግስጋሴ ለመግታት ቢፈልግ እንኳ ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል። ይሁንና ባልሞት ባይ ተጋዳይነት መንፈስ 'ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር' ተብሎ ሴት ወንዱ ከየመሥሪያ ቤቱ እና ማመምረቻ ተቋም ተነትቶ ለብለብ ሥልጠና እየተቀበለ ወደ ጦር ሜዳ ይላካል። ግዜው ዋይታ እና ምሬት በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ምድር ያስተጋባበት ወቅት

ነበር ብል ማጋነን አይመስለኝም። የብሔራዊ ውትድርና ምልመላ ሥርዓት እና ወግ አጥቶ በጉቦ እና ዘመድ የሚሰራበት ብሎም የጠሉትን ሰው ለማጥቃት እንደ ቅጣት የሚጠቀሙበት መድረክ ከሆነ ቆይቷል። ያገሪቱ ወጣት ተሚጦ ያለቀ ይመስል አባት ጦር የተባሉ ጡረተኛ እና ባብዛኛው አቅመ ደካማ የሆኑ የቀድሞ ወታደሮች እና መኮንኖች በጥድፊያ እየተጠሩ በጦርነቱ የመጀመሪያ ረድፍ እንዲዋደቁ ተደርጓል።

ብቃት በጎደለው እና በነቀዘ አስተዳደር አስራ ሰባት አመታት የተጓዘው የደርግ አስተዳደር የተከማቸ ሂሳቡን በኢትዮጵያ ጥፋት ኪሳራ እያወራረደ የነበረበት ዓመት ነበር - 1981።

ምንም አይሳናቸውም የተባሉት የደርጉ ቁንጮ በዙሪያቸው የኮለኮሏቸውን አድር ባይ ግለሰቦች ይዘው ከዚህ በላይ እንደማይጓዙ የተገነዘቡ ይመስል በየስብሰባው ፀያፍ ስድብ ሳይቀር እያወረዱ ተስፋ መቁረጣቸውን ሲያንፀባርቁ ታይተዋል። የወያኔ እና ሻቢያ አገዛዝ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ከመገመት አንፃር ትንሽ ቆይቶ የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ብላቴን ጦር ሠፈር ለሥልጠና እንደከተቱት አይነት የተንጠፋጠፈ የመልሶ መቋቋም እና መከላከል ጥረቶች እዚህ እና እዚያ ሲከናወኑ ታይቷል። ይሁንና - ጉዳዩ መልሶ እንደማይቋጭ ሁሉም ተረድቷል። በዚህ ሁሉ መካከል ብርቱ ስጋት ላይ የወደቀው ያገሪቱ ደህንነት ከወትሮው ጠበቅ ያለ የኬላዎች ቁጥጥር እና ቅኝት እንዲካሄድ ትዕዛዝ አስተላልፏል። የደርግ ባለስልጣኖች እንዳያመልጡ? ወይንስ ወያኔ ጥሶ እንዳይገባ? ተስፋዬ ወልደሥላሴ መልስ ሊሰጥበት የሚገባ ጥያቄ ነበር።

### 1981 የምድር ባቡር

ከአዲስ አበባ ድሬደዋ የሚጓዘው ባቡር ልዩ ማዕረግ ውስጥ ሽክ ባለ አለባበስ የተኮፈሰ ተጓዥ ተቀምጧል። ባቡሩ ማለዳ ተነስቶ ወደ ድሬ እየገሰገሰ ነው። በየከተሞቹ የተለመደ የፎርማታ ቆይታ ያደርጋል። ባቡሩ በዚያን ዕለት ሚኤሶ ላይ ባደረገው ቆይታ አንድ ነገር ተከስቷል። የኬላው አዛዥ ሻለቃ በለው ከአራት ባለሌላ ማዕረግ ወታደሮች ጋር ሆኖ (ይህ የምድር ጦር መኮንን በህይወት ያለ ሲሆን አሁን ባለበት ቦታ ለደህንነቱ ሲባል ትክክለኛ ስሙን አልጠቀምም) የተለመደ የፍተሻ ተግባሩን እያከናወነ ነበር።

ሻለቃ በለው ረጅም ቁመና ያለው ጥቁር ዳማ ፣ በዚያን ግዜ ሰላሳ አንድ ዓመት እድሜ እንዳለው የሚገመት ቆፍጣና መኮንን ነበር። ታጣፊ ክላሹን እንዳነገበ ወደ ልዩ ማዕረግ ዘው ሲል ወተት የመሰለ ነጭ ሸሚዝ ለብሶ ከተሳፈረው በዕድሜው ወደ አርባዎቹ መጀመሪያ ላይ ካለ ጎልማሳ ጋር አይን ላይን ይጋጫሉ። ተሳፋሪው ሻለቃ በለውን ሲያይ ከተኩስ እንዳመለጠ ድኩላ አይኑ ወዲያ ወዲህ መራወጥ ይዟል ፣ እንደ አይናፋርም እንደ ትሁትም እያደረገው … ይሁንና ለሻለቃ በለው ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ይሰጠዋል። ሻለቃው ቆቅ በመሰለ መርማሪ አይኑ ተሳፋሪውን ከግር እስከ ራሱ ገርምሞ አካባቢውን ጭምር መቃኘት ይዟል።

ከወትሮው የተለየ ነገር ባያገኝም በዚህ ከሰሜን ኢትዮጵያ የመጣ ለመሆኑ የተበጣ ግምባሩ የሚያረጋግጠው የልዩ ማዕረግ ተሳፋሪ ቁንጥንጥ ሁኔታ ግን ጥርጣሬ ገብቶት እየከነከነው ከባቡሩ ወርዶ ወደ ሚቀጥለው ግዳጅ ተሠማራ።

### ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን

በአገራችን ጋዜጠኛ እንዴት እንደሚቀጠር በትክክል መናገር ያስቸግራል። ጥሩ ድምፅ አለው ፣ ቁመናው ሸጋ ነው ተብለው ምንም አይነት የፅሁፍ እና አርትዖት ችሎታ የሌላቸው ግለሰቦች ይቀጠራሉ። በአፄው ዘመን ጭምር ከቤተ ክህነት የተመለመሉ ዲያቆናት ሁሉ በጋዜጠኝነት ተቀጥረው ይሠሩ ነበር። በደርግ ዘመን በፖለቲካ ታማኝነት ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች ወይም ህዝባዊ ድርጅቶች ታጭተው በአብዮታዊ አመራር የሚቀጠሩም ነበሩ። የፖለቲካ ድርጅቶች በበኩላቸው የኔ የሚሉትን ሰው በማስቀጠር የመገናኛ አውታሩን ለመጠቀም ጥረት ያደርጋሉ።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የተመሰከረ ችሎታ እና መደበኛ ስልጠና ያላቸው በሙያቸው ልብ-ሙሉ የሆኑ ጋዜጠኞች እንደ ነበሩ መጥቀስ አስፈላጊ ነው። የትምህርት ደረጃ መሥፈርት በጋዜጣ ላይ ወጥቶ የመግቢያ ፈተና እና ሌሎች ደረጃዎችን አልፈው ያለ አንዳች አድልዎ የሚቀጠሩ እንደነበሩም የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ያስታውሳል። የቅጥር አሠራሩን ይዞታ ስቃኝ  የተነሳሁበትን አጀንዳ ስለሚያስተኝ በዚሁ ልተወው።

ዛሬ ለማቅረብ በወሰንኩት እውነተኛ ታሪክ ዙሪያ የሚሽከረከረው ሰለሞን አስመላሽ በ1970ዎቹ አመታት ወደ ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ተቀጥሮ የመጣው በቢሮ ተላላኪነት ነበር። ሰለሞን በተክለ ሀይማኖት ሠፈር የአኢወማ ሊቀመንበር ሆኖ በመመረጥ ከአብዮቱ እና ከሰደድ ካድሬዎች ጋር የፀና ግንኙነት ፈጥሯል። ይሁንና ትምህርቱን ከስምንተኛ ክፍል በላይ ያልቀጠለ በመሆኑ በወቅቱ ለረባ ሥራ ሊታጭ አልበቃም። ከአደዋ ተነስተው ሥራ ፍለጋ

አዲስ አበባ መጥተው የቀሩት ወላጆቹ ተላላኪ ሆኖ ከሚቀጠር አንዱ ጋራዥ ተጠግቶ መካኒክነት ቢማር ይሻለው እንደነበር ሳይመክሩት የቀረ አይመስለኝም። ይሁንና ቴሌቭዥን መምሪያ በተላላኪነት ለመቀጠር መቻል ታላቅ ፖለቲካዊ ትርጉም ያለው ውጤት መሆኑን ሰለሞን እና በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ የሚያውቁት። እውነታው ለብዙዎች የተገለፀው ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ ብቻ ነበር።

ሰለሞን ቴሌቭዥን በተላላኪነት በተቀጠረበት ሰሞን ደርግ ፓርቲ ለመመሥረት ሽር ጉድ የሚልበት ነበር። ኢማሌድህ ከዚያም ኢሠፓአኮ ብሎም ኢሰፓ እያለ ደርግ የማይፈልጋቸውን እየጠራረገ የኔ የሚላቸውን እያቀፈ እያሞካሸ ድርጅታዊ መዋቅሮችን እያሰፋ ነው። በታማኝነቱ የተላላኪነት ሹመት ያተረፈው ሰለሞን በቴሌቭዥን መምሪያ ውስጥ ከተቀጠረ ጀምሮ በሚቋቋም የደርግ ፖለቲካዊ መዋቅር ውስጥ ሁል ግዜም ስሙ አለ። ሰለሞን ለደርግ ያለውን ታማኝነት ይበልጥ ለማረጋገጥ ደግሞ የተክለ ሀይማኖት ወጣት ማህበር ሊቀ መንበርነቱን መድረክ ይጠቀምበታል። ስብሰባ በመጥራት ፣ የአብዮቱን እርምጃ በመስበክ እና ፀረ-አብዮተኞችን በመመንጠሩ በኩል የነበረውን ንቁ ተሳትፎ በማሳየት። ሰለሞን በሲጋራ እና አልኮል የበለዘ ገፅታውን ቆጣ ቅጭም እያደረገ ያፈጠጠባቸው ፣ ያስፋራራቸው ጥቂት አልነበሩም። ሰለሞን አስመላሽ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ቢሆንም ተላላኪ ሆኖ ግን አልቀረም። በጥቂት ግዜ ውስጥ ቲቪ ሪፖርተር እና  ኢሰፓ ሲመሠረት ደግሞ ከመጀመሪያዎቹ ቀይ ደብተር ተቀባዮች አንዱ ሆኗል። በደርግ ፓርቲ ሹማምንት ዘንድ ሰለሞን ልዩ የሆነ ታማኝነት ተጎናፅፏል።

## የምድር ባቡር ጉዞ መልስ

ሻለቃ በለው የተለመደ የኬላ ቁጥጥር ሥራውን ቀጥሏል። ከአዲስ አበባ ወደ ድሬደዋ ከዚያም የሚመለሰውን ባቡር በቅጡ መፈተሽ ይዟል። ግዜው የጦርነት ነበር ፣ አገር ስጋት ላይ ወድቃለች እናም ሁሉም የነቃ ጥበቃ ማድረግ እንዳለበት ሻለቃ በለው ያምናል። እናም ከድሬደዋ አዲስ አበባ የሚመለሰውን የመንገደኞች መጓጓዣ ባቡር ለመቃኘት ማምሻውን በተጠንቀቅ እየጠበቀ ነው።

ባቡሩ ሚኤሶ ጣቢያ ሲቆም ሻለቃ እና አጃቢ ወታደሮቹ ፍተሻቸውን ጀመሩ። ታዲያ ወደ ልዩ ማዕረግ ሲገቡ አሁንም ያንን ጠዋት ወደ ድሬደዋ ሲጓዝ ያዩትን ሰው ብቻውን አንድ ክፍል ይዞ ያገኙታል። ሻለቃ እና ብቸኛው ተጓዥ ተፋጠጡ። ብቸኛው ተጓዥ የሙቁነጥነጥ ስሜት አድሮበታል። ሻለቃ በግለሰቡ ላይ ብርቱ ጥርጣሬ አድሮበት እንደነበር ያስታውሳል - ባንድ ቀን ድሬደዋ ደርሶ ለመመለስ ያውም በልዩ ማዕረግ ለምን አስፈለገ? ለምን ትንሽ ጥያቄ አላደረግለትም ሲል ሻለቃ ለራሱ ወሰነ። ወዲያውም “አንዴ ላናግርህ እፈልጋለሁ ፣ ከባቡሩ ውረድ” በማለት ሻለቃ በወታደራዊ ትዕዛዝ መልክ ጥያቄ ያቀርባል።

ብቸኛው መንገደኛ እንደ መደንገጥም እንደ መቆጣትም ብሎ “ምንድነው የምትጠይቀኝ? ለመሆኑ ማን እንደሆንኩ ታውቃለህ?” በማለት ደረቱን ማሻሸት ይጀምራል። ሻለቃ በዚህ ግዜ አንድ ነገር ያስተውላል - ወተት በመሰለው የብቸኛው ተጓዥ ነጭ ሸሚዝ ደረት ኪስ ዘልቆ ቀይ ደብተር ይታያል። ሻለቃ በለው የኢሰፓ አባል ባይሆንም የፓርቲ አባላት ቀይ ደብተር እንደሚሰጣቸው በደንብ ያውቃል። ‘ኦ ኢሰፓ ነህ?’ በማለት ሻለቃ ለራሱ ያሰላስላል።

ብቸኛው መንገደኛ የኢሰፓ አባል መሆኑን ለሻለቃው በማሳየት እንኳን ከባቡር አስወርዶ ሊጠይቀው እስካሁን የፈፀመው ክብረ ነክ መሆኑን ለማስገንዘብ ጭምር እየሞከረ ነበር። የሻለቃ በለው ባህሪ ግትርነት የታከለበት እና አገሩን የሚያፈቅር ፍፁም ወታደር መሆኑን ጥቂት ደቂቃ ከርሱ ጋር በመቆየት መመስከር ይቻላል። እና ብቸኛው ተሳፋሪ ለደቀነው ማስፈራሪያ ፍንክች ሊል አልቻለም። ይልቁንም “ግዜያችንን አታባክን ፣ በትህትና ተጠይቀህ የማትተባበር ከሆነ በግድ እናስወርድሀለን” በማለት ሻለቃ ውሳኔውን ፍርጥም ብሎ ነገረው።

“ለመሆኑ የፓርቲያችን ክብር እና አቋም ምን ያህል እንደሆነ ታውቃለህ?” ሲል በትግሪኛ አማርኛ (accent) ሻለቃን ሊያስፈራራ ያደረገው ሙከራ ውጤት አላስገኘም። ከዚህ ብቸኛ ‘የኢሰፓ’ መንገደኛ ጋር  መፋጠጡ ብዙ ውጤት እንደሌለው የተገነዘበው ሻለቃ አጃቢዎቹ አስገድደው እንዲያወርዱት በጥቅሻ ትዕዛዝ ይሰጣል። እናም ሰውየው በከፊል ተገፍትሮ በከፊል በራሱ ፈቃድ ከባቡር ላይ ወርዶ ወደ ምርመራ ክፍል ታጅቦ ይገባል። የመጀመሪያውን ጥያቄ ሻለቃ ከመሰንዘሩ በፊት ብቸኛው መንገደኛ ‘ኢሰፓው’ ስልክ እንዲቀርብለት በንዴት እያንባረቀ ይጠይቃል።

“የት ልትደውል?” ሲል ሻለቃ በትህትና ግን ረገጥ ባለ አነጋገር መልሶ ይጠይቃል።
“ጓድ ተስፋዬን ማነጋገር እፈልጋለሁ …አሁኑኑ” ይላል መንገደኛው … ‘ኢሰፓው’።
“መልካም ከዚያ በፊት ግን አጭር ጥያቄ እናቀርብልሀለን … ባቡር እንዳያመልጥህም ብትተባበረን ይመረጣል” ይላል ሻለቃ በለው። ስልኩ ይቅደም … የለም ምርመራው ይቅደም የሚለው አተካሮ ትንሽ ግዜ ቢወስድም - በመጨረሻ

ሻለቃው እንደማይበገር የተረዳው መንገደኛ ጥያቄ ለመቀበል ተገደደ። ይሁንና የሚሰጣቸው መልሶች ሁሉ ገዳዳ እና ድንጋጤ የተመላባቸው እምቢተኝነቱን የሚያሳይ ሆነ። አስገዳጅ የምርመራ ዘዴ እንዳይጠቀም የኢሰፓ ነገር አስፈሪው … እንዳይተው ብርቱ ምስጢር እና ተልዕኮ ያዘለ መንገደኛ መሆኑን አልተጠራጠረም።

ሻለቃ የግለሰቡን ማንነት ለመረዳት የተሻለ ዘዴ እያሰላሰለ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ወደቀ። በመካከሉ መንገደኛው የተሸከመው ሳምሶናይት በውስጡ ምን ምስጢር ሊኖረው እንደሚችል ለማወቅ ጉጉት አደረበት። እናም "ሳምሶናይትህን ክፈት" ሲል ሻለቃ ትዕዛዝ አስተላለፈ። እዚህ ላይ መንገደኛው ክፉኛ ደነገጠ ፣ ከተቀመጠበት ዘልሎ በመነሳት ሳምሶናይቱን ለቀም አድርጎ ማንም ከፍቶ የማየት ስልጣን እንደሌለው በዛቻ ጭምር አስጠነቀቀ። መንገደኛውን ጠምዝዞ ሳምሶናይቱን ለመቀበል ግዜ አልፈጀም ፣ ግብግብ ተነስቶ የነበረ በመሆኑም ከመንገደኛው ደረት ኪስ ውስጥ የነበረው ቀይ የኢሰፓ ደብተር መሬት ላይ ይወድቃል። ቀዩ ደብተር ተከፍቶ ሲነበብ የደብተሩ ባለቤት ስም ሰለሞን አስመላሽ የሚል ሲሆን የተለጠፈው ፎቶ ደግሞ ጭራሽ መንገደኛውን አይመስልም። ስሙን እንኳ ለመግለፅ ፈቃደኛ ሳይሆን የቆየው መንገደኛ በመጨረሻ ሰለሞን አስመላሽ መሆኑን የሚጠቁም የፓርቲ አባልነት መታወቂያ ተገኘበት። ሳምሶናይቱ ሲከፈት የተዘረገፈው የወረቀት መአት ግን ጉዳዩን ውስብስብ አደረገው።

በሳምሶናይቱ ውስጥ የረጅም ርቀት ሳተላይት ሬዲዮ ፣ በርከት ያለ ዶላር እና በተለይ ደግሞ የኤርትራው ተገንጣይ መሪ የኢሳይያስ አፈወርቂ ፎቶግራፎች ታጭቀዋል። ከዚህ በተጨማሪ ልዩ ልዩ ሪፖርት መሰል ፅሁፎች - በአረብኛ ፣ በእንግሊዝኛ እና በትግሪኛ በእጅ የተፃፉ ሰነዶች በጥንቃቄ ተጠርዘው ተይዘዋል።

ሻለቃ በፍጥነት እየተለዋወጠ የመጣው የዚህ ሰው ምስጢራዊ ማንነት ትንሽ ግራ አጋብቶት "ይኼ የፓርቲ ደብተር ያንተ አይመስልም - ፎቶው ፍፁም አንተን አይመስልም …" ሲል ይጠይቀዋል። መንገደኛው ነጭ ላብ ቢወርደውም አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ግን ፈቃደኛ አልሆነም።

በመጨረሻ ሻለቃ በለው ይኼ ብርቱ ምርመራ የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን በማረጋገጥ ግለሰቡን በእስር አሳድሮ ሁኔታውን ለወታደራዊ አለቆቹ በራዲዮ ሪፖርት ያደርጋል። የቅርብ አለቃው 'ይኼ የፓርቲ ጣጣ ስለሆነ ነገ ጠዋት ክፍለ ሀገሩ ፓርቲ ጽ/ቤት ወስደህ አስረክብ' ይለዋል።

አይነጋ የለ በነጋታው ማለዳ ሻለቃ በለው መንገደኛወን እስረኛ አስበ ተፈሪ ለሚገኘው የክፍለ ሀገሩ ኢሰፓ ጽ/ቤት በተለይ በግዜው የፓርቲው ፀሀፊ ለነበረው ተሰማ በላይ አስረክቦ ወደ ተለመደ ግዳጁ ይመለሳል። ሻለቃ በለው ወታደራዊ ግዳጁን ተወጥቶ ወደ ሌላ ግዳጅ መሠማራቱ ነበር። ጉዳዩ ግን በዚህ አልተደመደመም።

እስረኛውን አስበ ተፈሪ ኢሰፓ ጽ/ቤት ባስረከበ ዕለት ምሽት የክፍለ ሀገሩ ኢሰፓ ጽ/ቤት መኪና ሻለቃ በለው ባስቸኳይ እንደሚፈለግ የሚገልፅ መልዕክት ይዞ ከተፍ ይላል። ሻለቃ ለምን እፈለጋለሁ ብሎ ሳይጨነቅ በተላከው መኪና ተሣፍሮ ወደ ጽ/ቤቱ ያመራል። ከጽ/ቤቱ ሲደርሱ ሾፌሩ እየመራ ተሰማ በላይ ቢሮ ይዞት ይገባል።

ተሰማ በላይ ስልክ ላይ ነው። ሻለቃ በለው ወደ ቢሮ መዝለቁን ሲያይ ግን ወዲያውኑ "ጓዱ እዚህ ደርሷል … አንተ ራስህ አነጋግረው…" በማለት ስልኩን ለሻለቃ በለው "ስልክ ላንተ ነበር … ከአዲስ አበባ" ብሎ ያቀብለዋል። ደዋዩ ማን እንደሆነ እንኳ አልገለፀለትም።

በስልኩ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ እንግዳ ነው። "ጓድ ሻለቃ ያከናወንከው ተግባር የሚያስመሰግንህ ነው … ይሁንና ጉዳዩን እኛ እናጣራለን … ይኼ የኛ ሥራ ነው … ለአሁኑ እስረኛውን እንድትለቀው…" የሚል ቀጭን ትዕዛዝ። ሻለቃ በለው "ማን ልበል ጌታዬ?" ብሎ ጠየቀ።

"… ተስፋዬ ነኝ… እነዳልኩህ ባስቸኳይ እስረኛውን ለቀህ ወደ አዲስ አበባ በራሱ ግዜ ይምጣ…"።

"ተስፋዬ? …. እእእእእ … ተስፋዬ?" አለ ሻለቃ የቱ ተስፋዬ እንደሆነ ባለማወቅ።

ስልክ ደዋዩ ተስፋዬ ወልደሥላሴ  የደህንነቱ ሚኒስትር እንደሆነ ተሰማ ዝግ ባለ ድምፅ ለሻለቃ ይገልፅለታል። ሻለቃ በበኩሉ የደዋዩን ማንነት ከተረዳ በሁዋላ መልሱን እጥር ፍርጥም ባለ መልኩ ይሰጣል። "ጌታዬ እስረኛው በኔ ሥር አይደለም … ለፓርቲው አስረክቤያለሁ… መፍታትም መወሰንም የኔ ስልጣን አይደለም…" በማለት። ተስፋዬ በበኩሉ የሚችለውን ያህል ማስፈራራት ቢያደርግም ሻለቃው ፍንክች ሳይል በመጣበት ወደ ሰፈሩ ይመለሳል።

ጉዳዩ እንዲህ ሆኗል - ተሰማ በላይ እስረኛውን በሚመለከት የተጠናቀረውን አጠቃላይ ሪፖርት በቀጥታ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ደህንነት መምሪያ እና በደረጃ ለመንግስቱ ሃይለማርያም ይልካል። መንግስቱ በበኩሉ ጉዳዩን ተስፋዬ

ወልደሥላሴ አጣርቶ እንዲያቀርብለት ትዕዛዝ ይሰጣል። ተስፋዬ ስለ ግለሰቡ መታሠር መጀመሪያ ያወቀው በዚህ ሁኔታ ነበር የሚል ግምት አለ። በመንግስቱ ቤት እንደ ተስፋዬ ወ/ሥላሴ ያለ ታማኝ የለም።

ተስፋዬ እና እስረኛው ይተዋወቃሉ - የቤት ሥራ እየሠሩ ነበር። መንግስት ሳያውቀው ከተገንጣዮች ጋር ግንኙነት ፈጥሬ ነበር ብሎ እስር ቤት ከገባ በሁዋላ ተስፋዬ መናዘዙን ልብ ያደርጓል። ተስፋዬ እስረኛው እንዲፈታ እና አዲስ አበባ መሄድ እንዲፈቀድለት መጀመሪያ ያሳሰበው ተሰማ በላይን እንደ ነበር ሻለቃ ተገንዝቧል። ተሰማ በላይ የጉዳዩን ውስብስብነት የተረዳ ይመስላል እናም ተስፋዬ ላቀረበለት የፍቺ ጥያቄ የሰጠው መልስ "... ያሰርኩት እኔ አይደለሁም ... እኔ ልፈታው አልችልም" የሚል ነበር። የሻለቃ በለው ህልውና በተስፋዬ ወ/ሥላሤ እና በምስጢር እየተገናኛቸው ካሉት የአገር ጠላቶች ራዳር ውስጥ ገብቷል። ማንም ይሰረው ማን መንገደኛው ባለ ሰለሞን አስመላሽ የፓርቲ ደብተር ነፃ መለቀቅ አለበት።

ተስፋዬ ወ/ሥላሴ በተከታታይ እየደወለ ተሰማ በላይን ለማግባባት እና እስረኛውን ለማስፈታት ያደረገው ሙከራ ችግር ሳያስከትል አልቀረም። ተሰማ በላይ የደርግ አባል እንደመሆኑ የተስፋዬ መወራጨት ጥርጣሬ እንዲገባው አድርጎታል። እናም ጉዳዩን በቀጥታ ለመንግስቱ ደውሎ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል። መንግስቱ የተስፋዬን አካሄድ መረዳት የተቸገረ ቢመስልም ጉዳዩ በሌላ አካል ክትትል እንዲደረግበት ይወስናል። በዚህ መሠረት ጉዳዩ ሐረር ለሚገኘው ለምሥራቅ ሐረርጌ ኢሰፓ ፀሀፊ ለገብረየስ ወልደሀና ይተላለፋል። መንግስቱ ተፋጦ ከሚገኝበት አጣዳፊ የጦርነት ሥራ ተጨማሪ ይህን ጉዳይ ሥራዬ ብሎ መከታተል የሚችልበት ሁኔታ ውስጥ አልነበረም። ተሰማ በላይ ፀሀፊ የሆነበት ምዕራብ ሐረርጌ አዲስ መዋቅር እንደመሆኑ እንደዚህ አይነቱን ሀላፊነት ለመቀበል አቅሙ የለውም። ገብረየስ ወታደራዊ ኮሚሳር ሆኖ ብዙ ዘመን ያገለገለ ጠንካራ ወታደር እና ለመንግስቱ በነበረው ቀረቤታ በርካታ ወታደራዊ ሀላፊነቶችን ሲወጣ የቆየ ነበር። ዋናውን የምሥራቅ በር እንዲመራ የተመረጠው ለዚህ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሻለቃ በለው ከተስፋዬ ወ/ሥላሴ ጋር በስልክ በተመላለሱ ዕለት ማምሻውን ሌላ ከፍተኛ ባለሥልጣን ዘንድ ለመቅረብ በቅቷል። ድሬደዋ ላይ የታንከኛ ብርጌድ አዛዥ የነበረ በትውልዱ ትግራይ ወይም ኤርትራ የሆነ ብርጋዴር ጄነራል (በርሔ ወይም ተክሌ - በወቅቱ ይህን ጄነራል የምታውቁ ስሙን ልትገልፁ ትችላላችሁ) አንድ ራሱን ሆኖ በጂፕ መኪና ሲበር ሻለቃ በለው የፍተሻ ሥራ ከሚያከናውንበት የሚኤሶ ኬላ ይመጣል። ጄኔራሉ ያለ አንዳች አጀቢ በውድቅት ሌሊት ሲጣደፍ መምጣቱ ሻለቃ በለውን በጣም ገርሞታል። ሻለቃ በለው ካለበት ተጠርቶ ወደ ጄነራሉ ሲቀርብ "የያዝከውን ግለሰብ ካላንዳች ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ እንደትፈታ ልነግርህ ነው የጠራሁህ" ይለዋል። ሻለቃ በለው በዚህ እስረኛ ጉዳይ ይህ ሁሉ ትርምስ ለምን እንዳስፈለገ በተለይም ትላልቅ ሀላፊነት ላይ የሚገኙ ባለስልጣኖች በዚህ መልኩ መረባረባቸው አስገርሞታል። ጄኔራሉ ላቀረበው ጥያቄ ሻለቃ የሰጠው መልስ ግን ለተስፋዬ ወ/ሥላሴ በስልክ ከሰጠው የተለየ አልነበረም። ባጭሩ "እስረኛው በእኔ እጅ አይደለም...." የሚል ነበር። ጄነራሉ በበኩሉ "...ያልኩህን ባትፈፅም ዋጋህን በቅርቡ ታገኛለህ" የሚል ማስፈራሪያ ለሻለቃ በለው ሰጥቶ እና በቆመበት ጥሎት በመጣበት ጅፕ ብቻውን ወደ ድሬደዋ ከነፈ።

### ድሬደዋ

ሚኤሶ ላይ የተያዘውን እሥረኛ በሚመለከት የተፈጠረው ግርግር መንግሥቱ ሀይለማርያም በሰጠው አዲስ ትዕዛዝ ሌላ አቅጣጫ እንዲይዝ ሆኗል። እስረኛው ተፈቶ አዲስ አበባ ከመሄድ ይልቅ በከፍተኛ ጥበቃ ታጅቦ ወደ ድሬደዋ እንዲላክ እና በምሥራቅ ሐረርጌ ኢሠፓ እና ደህንነት ሥር ጉዳዩ እንዲመረመር ሆነ። አንባቢ እንዲገነዘብ የምፈልገው አንድ ነጥብ ይኖራል። የተያዘው እስረኛ የሻቢያ የስለላ መልዕክተኛ መሆኑን ከፍ ሲል ከተገለፀው ሁተታ መገመት የሚያዳግት አይመስለኝም። እና ትርምሱ በኢሰፓ እና መንግስቱ ብቻ ሳይሆን እነ ኢሳይያስ እና መለስ ጭምር ጉዳዩን በቅርብ እየተከታተሉ መሆኑን ነው። ተስፋዬ ወልደሥላሴ እና ሌሎች የውስጥ ትክሎች ሊጋለጡባቸው ተቃርቧል - ለሸአቢያም ሆነ ወያኔ ይህ በጣም ከፍተኛ አደጋ ነበር።

እስረኛው ድሬደዋ ሲደርስ አዲስ አበባ ላይ ደግሞ ሰለሞን አስመላሽ - የቀድሞው ተላላኪ ያሁኑ የቴሌቭዥን ፕሮግራም አቅራቢ ፣ የኢሠፓ ብርቅዬ ልጅ በቀጥጥር ሥር እንዲውል እና እሱም ድሬደዋ ተልኮ ጉዳዩ እንዲጣራ ተወሰነ። ሰለሞንን በኢሠፓ ነባር አባልነት የሚያውቁ ፣ ይልቁንም እንደ ልዩ የፓርቲ ታማኝ ካድሬ ይመለከቱት የነበሩ ሁሉ በሰለሞን ያውም ድሬደዋ ድረስ ተወስዶ መታሠር ግር ተሰኙ። ምን አጥፍቶ እንደታሠረ በይፋ የሚገልፅ ሰው ደግሞ የለም። በስህተት በተፈጠረ አንዳች ጉዳይ

ታስሮ እነደሆነ ብለው (የዚህን ፅሁፍ አቅራቢ ጨምሮ) ብዙዎቹ ገምተዋል። ምርመራው ገብረየስ ወ/ሀና ጥረስ ገባ - መውጫው እየጠበበ መጣ።

ገብረየስ ወልደሀና የእሥረኛውን ጉዳይ በቅርብ በመከታተል ግለሰቡ ድሬደዋ መጥቶ ከማን ጋር እንደተገናኘ ጭምር የሚደረገው ምርመራ ቀጠለ። መንግሥቱ ሀይለማርያም የገነባው የኢሠፓ ሥርዓት ምን ያህል ውስጡ እንደምስጥ ተበልቶ ማለቁን ሊገነዘብ የሚችልበት ተጨባጭ መረጃ እየተዘጋጀለት ነበር። ተስፋዬ ወልደሥላሴን ጨምሮ ብዙ ጄነራሎችን እና መኮንኖችን የሚያስበላ የምርመራ ውጤት እየተፈለፈለ ነበር። በሻቢያ እና ወያኔ የመሀል አገር አገልጋዮች ሠፈር የከፋ አደጋ አጠለለ። እነ ተስፋዬ ተርበተበቱ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አዲስ አበባ ላይ በደህንነቱ መሥሪያ ቤት ተጠናቅሮ የመጣ የሁለት ጎሳዎች ግጭት ዜና ለምሥራቅ ሐረርጌ ኢሠፓ ጽ/ቤት እንዲደርስ ይደረጋል። የደህንነት ጽ/ቤቱ ባወጣው ስልት መሠረት የምሥራቅ ሐረርጌ ባለሥልጣናት ከሥፍራው ተገኝተው ተቀሰቀሰ የተባለውን ይህን ከባድ የጎሳ ግጭት በግዜ እንዲያበርዱ ፣ የሁለቱንም ጎሳዎች ሽማግሌዎች እንዲያነጋግሩ ፕሮግራም ወጣ። የምሥራቅ ሐረር ኢሠፓ ፀሀፊ ገብረየስ ወ/ሀና የቡድኑ መሪ በመሆን ፣ የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ፣ የደህንነት ሀላፊ ፣ ፖሊስ አዛዥ እና ሌሎችም ጉዳዩ በቅርብ ይመለከታቸዋል የሚባሉ ሁሉ ሥፍራው እንዲጓዙ ተባለ። ድሬደዋ እንዲዛወር የተደረገውን እስረኛ ጉዳይ የሚያውቁ ባለሥልጣናት በሙሉ የዚህ ልዑክ አባል እንዲሆኑ ተመረጡ። ጉዞው በሄሊኮፕተር እንዲሆን ፕሮግራም ወጣ።

ተስፋዬ ወ/ሥላሤ ከተገንጣዮች ጋር በምስጢር ሲያከናውነው የነበረው ግንኙነት በአለቃው ዘንድ ሊጋለጥ ጫፍ ላይ ደርሷል። በዚህ ቅፅበት ግን እሱ በነደፈው የጎሳ ግጭት ሪፖረት የሽምግልና እና የአስተዳደር እርምጃ ለመውሰድ የተጋበዙት እነ ገብረየስ ወ/ሀና ግጭቱ አለ ወደተባለበት ለመድረስ ወደ ተዘጋጀላቸው ሄሊኮፕተር ገብተው ታጨቁ።

ሄሊኮፕተሩ ክንፉን እየወነጨፈ ያካባቢውን አቧራ ነስንሶ ከማኮብኮብያው አፈፍ ብሎ ወደ አየር ወጣ። ከፍ ከፍ ከፍ አለና ትንሽ እንኳ ሳይርቅ ብራቅ እንደመታው ያህል ፈነዳ እናም እንደጧፍ እየነደደ ወደ መሬት ተምዘገዘገ። ሁሉም ተሳፋሪዎች አለቁ - ሁሉም ፀጥ አሉ። አስታራቂም መርማሪም ልሳኑ ተዘጋ።

ሰባት ከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣናት የተፈጁበት ሄሊኮፕተር ድሬደዋ ላይ በፈነዳ ሳምንት ባልሞላው ግዜ ውስጥ ሰለሞን አስመላሽ ከድሬደዋ እሥር ቤት ተፈቶ ወደ መደበኛ ሥራው አዲስ አበባ ተመለሰ። በምን የተነሳ ሊታሠር እንደበቃ በቅርብ የሚያውቁት ሰለሞንን ሲጠይቁት ይሰጥ የነበረውን መልስ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ያስታውሳል። ሰለሞን ይል እንደነበረው "… አንዱ ሻቢያ ምርመራ ቶርች ሲገባ ሰለሞን አስመላሽ አባላችን ነው ብሎ በመዘባረቁ እስኪጣራ በሚል ሰበብ ነው የተያዝኩት… ኤርትራዊነት ጨርሶ እንደሌለኝ እየታወቀ ለምን ልታሠር እንደበቃሁ አይገባኝም…" ነበር የሚለው። ተላላኪው ሰለሞን አስመላሽ ትግሬ መሆኑን እንኳ የሚያውቁ ወይም ለዚያ አይነቱ መለያ ቦታ ሰጥተው የሚጨነቁ አልነበሩም።

በአፄው ዘመን የአሥመራ ከንቲባ የነበሩት (ሐረጎት አባይ ወይንም ስዩም ሐረጎት) ልጅ እንደ ነበረ የሚገመተው መንገደኛው እሥረኛ ግን የት እንደደረሰ ተስፋዬ ወልደሥላሴ ብቻ ነው ሊነግረን የሚችለው።

የኢሠፓ ብርቅዬ ልጅ ፣ የአኢወማ ምልምል ሰለሞን አስመላሽ ዛሬ የሰው በላውን 'አጋዚ' ታሪክ በቪዲዮ ፊልም እየመገበን ነው። ይኸው ሰለሞን አስመላሽ ነበር ወያኔ አዲስ አበባ እጅ በወደቀችባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ልዩ ዘገባ እና የነ ተፈራ ዋልዋ ኢንተርቪው አድራጊ ሆኖ ሽር ጉድ ሲል የነበረው።

ኑሮ እንደዚህ ነው። በተላላኪነት የተጀመረ ፀረ-አገር ተልዕኮ በሹምነት ተደርቦ እዚህ የሚያደርስ። ምን ያደርጋል ትምህርት ፣ ምን ያደርጋል ሙያ … ትግል ይሏል ይኼ ነው - የገደለሽ ገና ብዙ ይበላል።

የነ ገብረየስ  ወልደሀና ደም ግን በተስፋዬ ወልደሥላሴ እጅ ነው። ሹማምንቱ የተሳፈሩበት ሄሊኮፕተር ላይ ፈንጂ ለማጥመድ የዚያን ግዜ ለነ ሸአቢያ በጣም ቀላል ሥራ ነበር። እነ ጄኔራል (በርሔ ይሁን ተክሌ) ያንን ለማስፈፀም የሚያንሱ አልሆኑም። ወቅቱ የሞት የሽረት ጉዳይ ነበር።

ሻለቃ በለው የእስረኛውን ወደ ድሬደዋ መወሰድ ጉዳይ በቅርብ ይከታተል ነበር - ከተሰማ በላይ ዘንድ ብቅ እያለ ይጠይቃል።በመጨረሻ ላይ የደረሰው የሂሊኮፕተር እልቂት ድንገት የተፈጠረ አደጋ እንዳልሆነ ለመገመት ግዜ አልፈጀበትም። በጠፍ ጨረቃ ጂፑን ያለ አጃቢ እያሽከረከረ ከድሬደዋ የመጣው ጄኔራል '…የምልህን ካልሰማህ ዋጋህን ትቀበላለህ" ያለው ነገር አሁን ግልፅ ትርጉም ሰጥቶታል። እናም አጓጉል ሞት እንደሚጠብቀው አምኗል። አንዳች ሳያመነታ ወታደራዊ ብቃቱን ሊያረጋግጥ ወደሚችልበት ግምባር በራሱ ጥያቄ እና ውሳኔ ማንም ሊያውቅ በማይችልበት ሁኔታ ወጥቶ ነጎደ። ለሀገር እና ለህዝብ ደህንነት የተሰለፉ ጀግኖች እንደዚህ እየተዋከቡ እና ባገር በቀል ረጃጅም ሙጃዎች እየተዋጡ አልቀው ነው ዛሬ ኢትዮጵያ የወያኔ … የአጋዚ መፈንጫ የሆነችው።

ተስፋዬ ወልደሥላሴ የሥራ ባልደረቦቹን እንዲህ እንደ ቄራ ከብት እያሳረደ የት ለመድረስ ፈልጎ እንደነበር ማወቅ ያስቸግራል። ለወያኔ እና በይበልጥ ደግሞ ለሻቢያ ስለዋለው ውለታ የተከፈለው ወሮታ የለም። በሀፍረት እና ባደፈ ታሪክ ተጀቡኖ ግማሽ አካሉ መቃብር ወርዷል - በድን አካል ይዞ እየተንጠራወዘ መሆኑ ካለ ያህል አይቆጠርምና።

ተላላኪው ጋዜጠኛ ግን የሕይወት ዕጣ የጣለችበትን ዕዳ ክፍሎ ያበቃ አይመስለኝም።